Seattle Public Utilities

# North Thornton Natural Drainage Systems

FREQUENTLY ASKED QUESTIONS

# ኖርዝ ቶርንቶን (North Thornton) የተፈጥሮ የፍሳሽ ማስወገጃ ስርአቶች ተደጋግመው የሚነሱ ጥያቄዎች

## የፕሮጀክት አጠቃላይ እይታ እና ግቦች

**የሲያትል የህዝብ መገልገያዎች (SPU) ይህንን ፕሮጀክት ወደ ሰፈሬ የሚያመጣው ለምንድነው?**

በየአመቱ ከ12 ሚሊዮን ፓውንድ በላይ ብክለት ወደ ውሃ አካሎቻችን በዝናብ ውሃ ፍሳሽ ይወሰዳል። በሰፈርዎ ያሉ ጠንካራ የመሬት ገጽታዎች ላይ የሚያርፈው የዝናብ ዉሃ-እንደ ጣሪያዎች፣ ጎዳናዎች፣ እና የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች – በመጨረሻም ወደ ዋሽንግተን ሀይቅ እና ወደ ፑጀት ሳውንድ የሚፈሰው፣ ከመግባቱ በፊት ጎጂ በካዮች እያነሳ ወደ ቶርተን ክሪክ (Thornton Creek) ሊገባ ይችላል። በካዮቹ መርዞች ዓሦችን፣ የዱር አራዊትን፣ እና ሥነ ምህዳራችንን ሊጎዱ ይችላሉ። የሲያትል የህዝብ መገልገያዎች (SPU) የውሃ ጥራትን ለማሻሻል፣ የተፋሰሱ ችግሮችን ለመቀነስ፣ እና ሌሎች የማህበረሰብ ጥቅሞችን ወደ ሰፈርዎ ለማምጣት የሚያግዝ ፕሮጀክት ላይ እየሰራ ነው።

**ተፈጥሯዊ የፍሳሽ ማስወገጃ ዘዴዎች ምንድ ናቸው?**

የተፈጥሮ የፍሳሽ ማስወገጃ ዘዴዎች ጥልቀት የሌላቸው በመኪና የመንገድ ዳር ክፍተት ላይ የተገነቡ ናቸው (በመንገዱ ጠርዝ እና በንብረት መስመር መካከል ያለው የህዝብ ቦታ)። የተበከለውን የዝናብ ውሃ በጊዜያዊነት ለመያዝ እና ለማጣራት በልዩ አፈር እና ጥልቅ ሥር በሰደዱ ተክሎች የተሞሉ ናቸው።

**የፕሮጀክቱ ግቦች ምንድን ናቸው?**

ይህ ፕሮጀክት የተፈጥሮ የፍሳሽ ማስወገጃ ሥርዓቶች (NDS) አካል ሆኖ በ *የሲያትል የውሃ መንገዶችን ለመጠበቅ ዕቅድ* በአጋርነት የሚሰራ ፕሮግራም ነው፣ ተነሳሽነቱ ለሚከተሉት ዓላማዎች ነው:

- የተፈጥሯዊ የፍሳሽ ማስወገጃ ዘዴዎች (NDS) መትከል በሚቻልበት፣ በቶርንቶን ክሪክ (Thornton Creek) እና በዋሽንግተን ሐይቅ ያለውን የብክለት መጠን ለመቀነስ የተፈጥሮ የፍሳሽ ማስወገጃ ዘዴዎችን መገንባት እና የፍሳሽ ማስወገጃ ሥርዓትን ማሻሻል።
- የውሃ መውረጃ ችግሮችን መቀነስ፣ የትራፊክ ፍጥነት ማረጋጋት፣ አዳዲስ ዛፎችን፣ እና ተጨማሪ አረንጓዴ ቦታዎችን ጨምሮ ሌሎች የማህበረሰብ ጥቅማ ጥቅሞችን መስጠት።

## የፕሮጀክት ምርጫ

**ሰፈሬ እንዴት ተመረጠ?**

የሲያትል የህዝብ መገልገያዎች (SPU) በአሁኑ ጊዜ በመላ ሲያትል በበርካታ የከተማ ተፋሰሶች ውስጥ የተፈጥሯዊ የፍሳሽ ማስወገጃ ዘዴዎች (NDS) ፕሮጀክቶች ላይ እየሰራ ነው፣ *የቶርንቶን*፣ *ሎንግፌሎው*፣ እና *የፓይፐርስ ክሪክ* ተፋሰሶችን ጨምሮ። *የሰሜን ቶርንተን የተፈጥሮ ፍሳሽ ስርዓት (NTNDS)* ፕሮጀክት በሰሜናዊ የቶርተን ክሪክ ቅርንጫፍ ውስጥ ያለውን ብክለት በመቀነስ ላይ ያተኮረ ነው። የፕሮጀክቱ ቦታ ሰሜናዊውን የቶርንተን ክሪክ (Thornton Creek) ተፋሰስን ያጠቃልላል።

**የሲያትል የህዝብ መገልገያዎች (SPU) የትኞቹ ብሎኮች እንደሚመርጥ እንዴት**

የሲያትል የህዝብ መገልገያዎች (SPU) ከፍተኛውን የውሃ ጥራት ጥቅም የምንሰጥሰጥባቸውን የፕሮጀክት ቦታዎችን ይመርጣል። እንዲሁም ስጋቶችን ለመቅረፍ እና በርካታ ጥቅሞችን ለማቅረብ ከሌሎች የከተማ

**ይወስናል?**

ክፍሎች እና ከማህበረሰቡ ጋር ለመስራት አጋጣሚዎችን እንፈልጋለን (ለምሳሌ፡ የታቀደ መንገድ ወይም የእግረኞች ማሻሻያ ወይም የውሃ ፍሳሽ ችግሮችን ለመቀነስ)።

አንድን ጣቢያ የበለጠ ወይም ያነሰ ምቹ ሊያደርጉ የሚችሉ ሌሎች ምክንያቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ:

- በአቅራቢያው ያሉ አካባቢዎች አሉታዊ ሁኔታዎች (ገደላማ ተዳፋት፣ ከፍተኛ የከርሰ ምድር ውሃ፣ ወይም የተበከሉ ቦታዎች)
- ባሉ ነባር ዛፎች ላይ ሊያመጡ የሚችሉ ተፅዕኖዎች
- አሁን ያሉ የአፈር ሁኔታዎች
- አሁን ያሉ መገልገያዎች አካባቢ እና ሁኔታ
- የማህበረሰብ ግብአት
- አሁን ያለው የህዝብ መንገድ ስፋት
- የመኪና መንገዶች መገኘት
- አሁን ያለው የመኪና ማቆሚያ መጨናነቅ እና ከመንገድ ውጭ የመኪና ማቆሚያ መገኘት
- የፕሮጀክት ግንባታ፣ ክወና፣ እና የጥገና ወጪዎች

## የጊዜ መስመር

**የዚህ ፕሮጀክት የጊዜ ሰሌዳ ስንት ነው?**

በ2020፣ በፕሮጀክቱ አካባቢ ያሉትን ሁኔታዎች መርምረናል እና ቀደምት የፕሮጀክት እቅድ ማውጣትን ለማሳወቅ የማህበረሰብ የዳሰሳ ጥናት አካሂደናል። እ.ኤ.አ. በ 2021 እና በ 2022 መጀመሪያ ላይ፣ የተፈጥሮ የፍሳሽ ማስወገጃ ስርዓቶችን የማስገባት አዋጭነት ለመረዳት እና የት የት ጋ የበለጠ ጠቃሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ ቴክኒካዊ ትንታኔዎችን ቀጥለናል። በ2022ቱ ወቅት፣ የመጨረሻውን የብሎክ ምርጫ እና ለማህበረሰብ ጥቅም ተጨማሪ እድሎችን ለማሳወቅ ተለይተው በታወቁ ብሎኮች ከቀደምት እቅድ ማውጣት ላይ የማህበረሰብ የዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ ያለውን መረጃ እንጠቀማለን። በ2023ቱ ወቅት እና በ2024 መጀመሪያ ላይ፣ የመጨረሻውን ዲዛይን ለማሳወቅ ከማህበረሰቡ ጋር የምናደርገውን ግንኙነት እንቀጥላለን። ግንባታው በ2024 ተጀምሮ በ2025 መጨረሻ ያልቃል ብለን እንጠብቃለን።

**የእኔ ብሎክ የተፈጥሮ የፍሳሽ ማስወገጃ ዘዴን ለመገንባት የተመረጠ እንደሆነ መቼ አውቃለሁ?**

በእቅድ ዝግጅቱ ወቅት፣ የተፈጥሯዊ የፍሳሽ ማስወገጃ ዘዴዎች ቦታዎች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከማድረጋችን በፊት በቴክኒካል አዋጭነት ላይ ተመስርተን ብቃት ያላቸው ቦታዎችን እናጠና እና የማህበረሰብ ግብአት እንሰበስባለን። በ2022 መጨረሻ አካባቢ ወይም በ2023 መጀመሪያ አካባቢ ስለ አካባቢ ምርጫ ተጨማሪ ዝርዝሮችን እናቀርባለን።

## የማህበረሰብ ግብአት

**የሲያትል የህዝብ መገልገያዎች (SPU) ከነዋሪዎች ምን ያህል ግብአት ይፈልጋል?**

የማህበረሰብ ተሳትፎ ለኛ ጠቃሚ ነው። በእቅድ፣ በንድፍ፣ እና በግንባታ ደረጃዎች ወቅት ከእርስዎ ጋር እንመካከራለን። በእቅድ ዝግጅቱ ወቅት፣ ከእርስዎ እና ከጎረቤቶችዎ ስለ ልዩ ስጋቶች እና ፍላጎቶች ማወቅ እንፈልጋለን። እንደ የዳሰሳ ጥናቶች፣ በመስመር ላይ እና በአካል ያሉ ክስተቶችን፣ እና በተለዩ ብሎኮች ውስጥ ከሚኖሩ፣ ከሚሰሩ፣ ወይም ከሚመላለሱ ባለድርሻ አካላት ጋር ስብሰባዎችን በማድረግ፣ የመሳሰሉ መሳሪያዎችን በመጠቀም ከእርስዎ መረጃ እንሰበስባለን። እንደ ኢሜይል፣ በራሪ ወረቀቶች እና *የፕሮጀክቱ ድህረ ገጽ* ያሉ መሳሪያዎችን በመጠቀም እናሳውቅዎታለን።

**የሲያትል የህዝብ መገልገያዎች (SPU) የማህበረሰብ አስተያየትን እንዴት ሊጠቀምበት ነው?**

በተቻለ መጠን በመጨረሻዎቹ ውሳኔዎች ላይ የማህበረሰብን አስተያየት እናካትታለን። ሊሆኑ የሚችሉ ቦታዎች ከተገመገሙ፣ የሲያትል የህዝብ መገልገያዎች (SPU) የፕሮጀክት ቦታዎችን ይመርጣል እና በንድፍ እና በግንባታ ደረጃዎች ውስጥ ከነዋሪዎች ጋር ፍላጎቶቻቸውን ለማስተባበር እና በተቻለ መጠን በእነዚህ ብሎኮች የግንባታ ተፅእኖዎችን ለመቀነስ ከነዋሪዎች ጋር ይሰራል።

## የፕሮጀክት ተጽእኖ እና ጥገና

**ተፈጥሯዊ የፍሳሽ ማስወገጃ ዘዴዎች ከተገነቡ በኋላ ምን ይመስላሉ?**

በመኖሪያ ሰፈሮች ውስጥ የተፈጥሮ የፍሳሽ ማስወገጃ ዘዴዎች በመኪና የመንገድ ዳር ክፍተት (በመንገዱ ጠርዝ እና በንብረት መስመር መካከል ያለው ክፍተት) የተገነቡ ናቸው። ፕሮጀክቶቹ የተለያዩ የአፈር ዓይነቶችን እና እፅዋትን በማጣመር ከመኪና መንገድ እና ከመኪና ማቆሚያ ስፍራዎች የታጠቡ ቆሻሻዎች/በካዮች የሚይዝ እና የሚሰብር "ማጣሪያ" ለመፍጠር ይጠቀማሉ።

እያንዳንዱ የተፈጥሯዊ የፍሳሽ ማስወገጃ ዘዴዎች (NDS) ፕሮጀክት በማደግ ላይ ባሉ ተክሎች የተገነባ ስለሆነ፣ መልካቸው በጊዜ ሂደት ይለወጣል። ብዙውን ጊዜ ሙሉ በሙሉ ለማደግ ከሶስት እስከ አምስት ዓመታት ይወስዳሉ። በግንባታው ወቅት የተተከሉት ሳሮች፣ ቁጥቋጦዎች፣ እና ዛፎች ያድጋሉ እና የአትክልት ቦታው ሲያድግ ይለወጣሉ። በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ዓመታት፣ በተፈጥሯዊ የፍሳሽ ማስወገጃ ዘዴዎች የሚሰበሰበው የዝናብ ውሃ የበለጠ የሚታይ ይሆናል። እፅዋቱ ካደጉ በኋላ፣ ውሃው ብዙም አይታይም። ደግሞም እፅዋቱ በዓመቱ ውስጥ በተለያዩ ወቅቶች የተለያየ መልክ ይኖራቸዋል።

**በተፈጥሮ የፍሳሽ ማስወገጃ ዘዴዎች ውስጥ ውሃ አያለሁ?**

በማዕበል ወቅት፣ እያንዳንዱ የፍሳሽ ማስወገጃ ሥርዓት ለጊዜው እስከ 12 ኢንች ውሀ ይይዛል፣ ከዚያም ዝናቡ ካበቃ ከ24 ሰአታት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ይፈስሳል። በተከታታይ የሚመጡ አውሎ ነፋሶች/ዝናብ ወይም ትልቅ ማዕበል ሲኖሩ፣ የውሃው መጠን ከፍ እና ዝቅ ይላል፣ ይህም የፍሳሽ ማስወገጃ ስርዓቱ በትክክል እየሰራ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ነው።

**በጣም ብዙ ዝናብ ቢዘንብ የውሃ ፍሳሽ ማስወገጃ ስርዓቱ ሞልቶ ቢፈስስ?**

ተፈጥሯዊ የፍሳሽ ማስወገጃ ዘዴዎች አውሎ ነፋሱ ካለፈ በ 24 ሰአታት ውስጥ ሙሉ በሙሉ እንዲፈስ ተደርገው የተሰሩ ናቸው። ስርዓቱ በአንድ ጊዜ ሊይዘው ከሚችለው በላይ ውሃ ካለ፣ ከስርአቱ የሚወጣውን ከመጠን በላይ የሆነዉን የዝናብ ውሃ በአቅራቢያው ወደ ሚገኝ ቧንቧ፣ ቦይ፣ ወይም የአውሎ ንፋስ ፍሳሽ ሲፈስ ማየት ይችላሉ።

**ጣቢያው በ 24 ሰዓታት ውስጥ ካላፈሰሰ ምን ይከሰታል?**

የሲያትል የህዝብ መገልገያዎች የአሰራር ምላሽ ማዕከል (SPUORC) ሰዎች እንዲደውሉ እና የፍሳሽ ማስወገጃ ጉዳዮችን እንዲያሳውቁ የ24/7 የቀጥታ የስልክ መስመር ይሰጣል። በቤትዎ አቅራቢያ ያለው ስርዓት በትክክል ካልፈሰሰ ወይም ጥገና የሚያስፈልገው ከሆነ፣ እባክዎን ይደውሉ: (206) 386-1800።

**ስርዓቱን የመጠገን ሃላፊነት ያለው ማነው?**

የሲያትል የህዝብ መገልገያዎች (SPU) ለሁሉም ስርዓቶች የጥገና ፍላጎቶች፣ ማለትም ውሃ ማጠጣት፣ አረም ማረም፣ እና አጠቃላይ እንክብካቤን ጨምሮ ሃላፊነት አለበት። የሲያትል የህዝብ መገልገያዎች (SPU) እንደ አስፈላጊነቱ ዛፎችን እና ቁጥቋጦዎችን ይቆርጣል። እርስዎ ምንም አይነት ጥገና እንዲያደርጉ አይጠየቁም። በእርግጥ፣ ነዋሪዎች የስርዓቶችን መሥራት እንዲጠብቁ ከተፈጥሯዊ የፍሳሽ ማስወገጃ ዘዴዎች ውጭ መቆየታቸው አስፈላጊ ነው። ተክሎች በጊዜ ሂደት ያድጋሉ እና የተክሎች ድብልቅነት ሊለወጥ ይችላል፣ ነገር ግን ይህ የስርዓቱን ተግባር አይጎዳውም።

**ይህ ሥራ አሁን ባሉት ተክሎች እና ዛፎች ላይ ምን ተጽዕኖ ያሳድራል?**

በተቻለ መጠን፣ የፕሮጀክቱ ቡድን ባደጉ ዛፎች ላይ የሚኖረውን ተጽእኖ ይቀንሳል። ምናልባት ዛፎች በሚጎዱበት ጊዜ፣ ለእያንዳንዱ የተወገደ ዛፍ በሁለት አዲስ ዛፎች እንተካለን። አንዳንድ ትናንሽ ወይም ጤናማ ያልሆኑ ዛፎች ቦታ መቀየር ወይም መተካት ሊኖርባቸው ይችላል። በግንባታው ወቅት፣ ዛፎችን መከላከል ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው።

**የተፈጥሯዊ የፍሳሽ ማስወገጃ ዘዴዎች በእኔ ምድር ቤት ጎርፍ እንዲሆን ወይም በቤቴ ዙሪያ የውሃ ፍሳሽ ችግር ይፈጥራል?**

ተፈጥሯዊ የፍሳሽ ማስወገጃ ዘዴዎች የተነደፉት የዝናብ ውሃን በቀጥታ ወደ መሬት ውስጥ ለማስገባት ወይም ከመሬት በታች "የውሃ ፍሳሽ" ቱቦ ውስጥ እንዲገቡ ነው እንጂ ወደ ጓሮዎች ወይም የታችኛው ምድር ቤት አይደለም። የሲያትል የህዝብ መገልገያዎች (SPU) የዝናብ ውሃን በቀጥታ ወደ መሬት ውስጥ ሰርጎ ለመግባት ምቹ የሆኑ ቦታዎችን ለማግኘት የአፈር ምርመራ መረጃን ይጠቀማል። ጥሩ የአፈር ሁኔታዎች ከሌሉ፣ ከመሬት በታች ያለው የውኃ ፍሳሽ ቱቦ ውኃ ለመሰብሰብ ይጠቅማል። አስፈላጊ ከሆነ፣ ለተጨማሪ ጥበቃ ከመሬት በታች ባለው መስመር መከላከያ በማድረግ ጣቢያው ሊነደፍ ይችላል።

**ይህ ፕሮጀክት በመንገድ የመኪና ማቆሚያ ቦታ ላይ ምን ተጽዕኖ ይኖረዋል?**

ይህ ፕሮጀክት በመንገድ የመኪና ማቆሚያ ቦታ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል። የሲያትል የህዝብ መገልገያዎች (SPU) መኪና ማቆሚያ እና ከመንገድ ወደ ቤቶች እና ንብረቶች መድረስ ለማህበረሰብ አባላት በጣም አስፈላጊ መሆኑን ያውቃል። በእያንዳንዱ የፕሮጀክት ቦታ ላይ በመኪና ማቆሚያ ላይ ያለውን ተጽእኖ በጥንቃቄ እንመለከታለን። እንዲሁም ከመንገድ ወጣ-ያለ በአቅራቢያው የመኪና ማቆሚያ ሁኔታን እና መገኘቱን እንገመግማለን።

**ይህ ፕሮጀክት ትንኞችን ይስባል?**

አይደለም፣ ትንኞችን አይስብም። ትንኞች የቆመ ውሃ ያስፈልጋቸዋል (የወፍ መታጠቢያዎች፣ አሮጌ ጎማዎች፣ የውሻ ውሃ ጎድጓዳ ሳህኖች፣ ወዘተ ውስጥ የሚገኙ)። ተፈጥሯዊ የፍሳሽ ማስወገጃ ዘዴዎች ያለማቋረጥ እንዲፈስሱ እና ውሃ እንዲንቀሳቀስ ለማድረግ የተነደፉ ናቸው።

**ውሃው እዚህ ተሰብስቦ እና ሲከማች ልጆቼ እና የቤት እንስሳዎቼ ደህና ይሆናሉ?**

ተፈጥሯዊ የፍሳሽ ማስወገጃ ዘዴዎች የተነደፉት ደህንነትን ግምት ውስጥ በማስገባት ነው። በተለምዶ አውሎ ነፋሱ ካለቀ በ24 ሰአታት ውስጥ ይፈስሳሉ፣ እና በአብዛኛዎቹ ሁኔታዎች፣ ይበልጥ ፈጣን ይሆናል። ለስርዓቱ ጤና እና ተግባራዊነት፣ ሰዎች እና የቤት እንስሳት ወደ ተፈጥሯዊ የፍሳሽ ማስወገጃ ዘዴዎች እንዳይገቡ እንጠይቃለን።

**ጥገና የሚያስፈልግ ከሆነ ማንን ማግኘት እችላለሁ?**

በቤትዎ አጠገብ ያለው የተጠናቀቀው ፕሮጀክት በአግባቡ ካልፈሰሰ ወይም ጥገና የሚያስፈልገው ከሆነ እባክዎን በ: (206) 386-1800 ይደውሉ።

# የብሎክ ምርጫ ሂደት እና የጊዜ መስመር

| የብሎኮች ብዛት | የፕሮጀክት ደረጃዎች | የጊዜ መስመር |
|---|---|---|
| | ሰሜን ቶርንተን (Thornton) ተፋሰስ | **2020 እና 2021**<br>▪ የፕሮጀክቱ ቡድን የጥናት ቦታውን ገምግሟል እና የተፈጥሮ ፍሳሽ ማስወገጃ ዘዴዎችን ለመገንባት ብሎኮችን ለይቷል<br>▪ የፕሮጀክት ቡድን ለማህበረሰብ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች እና ስጋቶች የዳሰሳ ጥናት አድርጓል (2020) |
| 34 | ሊሆኑ የሚችሉ ብሎኮች | **2021-2022 መጀመሪያ**<br>▪ የፕሮጀክት ቡድን የተፈጥሮ ፍሳሽ ማስወገጃ ዘዴዎች በጣም ጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉበትን ቴክኒካል ጥናቶችን ተመልክቷል። |
| 22 | ሊሆኑ የሚችሉ ብሎኮች | **የካቲት–ግንቦት 2022**<br>▪ የፕሮጀክት ቡድን የብሎኮችን ምርጫ ለማጥበብ እና ስለ ማህበረሰብ ጥቅሞች እድሎች ለማወቅ የዳሰሳ ጥናት ያካሂዳል (ሚያዝያ/ግንቦት 2022)<br>▪ የፕሮጀክት ቡድን የተፈጥሮ የውሃ ፍሳሽ ስርዓት ጽንሰ-ሀሳባዊ ንድፎችን ያዘጋጃል |
| 13 | የእጅግ ከፍተኛ ጥቅም ብሎኮች | **ግንቦት–ታህሳስ 2022**<br>▪ የፕሮጀክት ቡድን ቀደምት ዲዛይን በማጠናቀቅ የውሃ ጥራት እና የማህበረሰብ ጥቅሞችን የሚሰጡ ብሎኮችን ይመርጣል<br>**2023-2024 መጀመሪያ** |
| 13 | ንድፍ እና ግንባታ | **2023-2025**<br>▪ የንድፍ እቅዶች ሲጠናቀቁ የፕሮጀክት ቡድን ለጎረቤቶች ያሳዉቃል<br>▪ የፕሮጀክት ቡድን የግንባታ መረጃን ለማህበረሰቡ ያካፍላል |

If you need this information about the North Thornton Drainage Systems project translated, please call (206) 462-9045.

**Amharic**

ስለ ሰሜን ቶርንተን (North Thornton) የተፈጥሮ ፍሳሽ ሥርዓት ፕሮጀክት መረጃ እንዲተረጎም ከፈለጉ፣ እባክዎን (206) 462-9045 ይደውሉ።

**Arabi**

إذا كنت بحاجة إلى هذه المعلومات حول مشروع شمال Thornton لأنظمة الصرف الطبيعية مترجمة، فيرجى الاتصال ب 462-9045 (206) .

**Chinese Traditional**

如果您需要 Thornton 溪北端支流自然排水系統項目信息的翻譯版本，請致電 (206) 462-9045。

### Korean

North Thornton 자연 배수 시스템 프로젝트에 관한 번역된 정보가 필요한 경우, (206) 462-9045 로 전화하십시오.

### Russian

Если вам нужен перевод информации о проекте Естественных дренажных систем северной части реки Thornton (North Thornton Natural Drainage Systems), пожалуйста, позвоните по телефону (206) 462-9045.

### Somali

Haddii aad u baahan tahay macluumaadka ku saabsan Mashruuca Nidaamyada Biyo-mareenka Dabiiciga ah (Natural Drainage Systems) ee North Thornton oo la turjumay, fadlan wac (206) 462-9045.

### Spanish

Si necesita la traducción de la información del proyecto del Sistema de drenaje natural de North Thornton, llame al (206) 462-9045

### Tigrinya

እንተደአ ነዚ ናይ ሰሜናዊ ቶርቶን (North Thornton) ተፍጥሮኣዊ ስርዓት መወገዲ ፈሳሲ ሓበሬታ ብትርጉም ክትረኽቦ ደሊኻ፡ ብኽብረትካ ናብ (206) 462-9045ደውል።

### Vietnamese

Nếu quý vị cần hỗ trợ dịch thông tin về dự án Hệ Thống Thoát Nước Tự Nhiên North Thornton, xin vui lòng gọi ((206) 462-9045

## ጥያቄዎች? የሲያትል የህዝብ መገልገያዎችን ይገናኙ

**ኬቲ ዊልሰን (Grace Manzano)** **የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ**
**Grace.Manzano@seattle.gov** **(206) 462-9045**

የበለጠ ይወቁ እና ለፕሮጀክት ማሻሻያ በ: www.seattle.gov/utilities/NorthThorntonNDSይመዝገቡ